የኢትዮጵያ ሕዝብ ብሄራዊ ፓርቲ
ETHIOPIAN PEOPLE NATIONAL PARTY

# ፋኖ

_ *የካቲት 3 2011 ዓ ም*

*የጥቅላይ ሚኒስተር አብይና የአቶ ለማ መገርሳ ድብቅ አጀንዳ ይፋ ሆነ !!*

ወያኔ እጅ እግሩ ተወላግዶ ከመቀሌ እንዲታቀብ የተደረገው በኢትዮጵያውያን መራራ ትግል እንጂ ዛሬ እነ ዶር አቢይና ለማ መገርሣ እንደሚሉት አለመሆኑን መላ የኢትዮጵያ ሕዝብ አሳምሮ የሚያውቀው ነው። ለአስተዋጾው ግንባር ቀደም ሆነው የተሰለፉት ቄሮ፣ፋኖ እና የጎበዝ አለቃ ናቸው። እነዚህ ሦስቱ ተቃዋሚዎች በተለያዩ ዘዴ እየተገናኙ ፀረ ወያኔ ትግላቸውን በማፋፋም ኅብረታቸውን አሳይተው ነብር። ለዚህ ተጨባጭ ማስረጃ ቢያስፈልግ የአማራ ወጣቶች የኦሮሞን ‹እሬቻ‹ በዓል ለማክበር ወደ ቢሾፍቱ በመጓዝ በዓሉን ሲያከብሩ ከኦሮሞ ጎን ተሰልፈው እንደተሰው ቄሮዎች ምስክር ናቸው፣ በተመሣሣይ መልኩ በርካታ የኦሮሞ ቄሮዎች ወደ አማራ ክልል በመጓዝ ጣና ሐይቅን የወረረውን እምቦጭ አረምን አርመዋል፣ የዕለቱ መፈክር **ጣናን ኬኛ፥ ጎጃም ኬኛ፥ጎንደር ኬኛ፡ ጣና የኛ ነው፣ ጎጃም የኛ ነው፣ ጎንደር የኛ ነው: ሲሉ የአማራም ወጣቶች ሐረር ኬኛ ባሌን ኬኛ፣ኦሮሚያን ኬኛ « የሚል ምላሽ ሲሰጡ ነበር።**ለዚህ እንቅስቃሴ የኦሮሞ ሕዝብ ነቅናቄ ለኢትዮጵያ አንድነት ያደረገው አስተዋጽኦ በጣም ሰፊ ነው። የሁለቱ ወጣት ኃይሎች ግንኙነት ያስደነገጠው ወያኔ እሳትና ጭድ ብሎ ፍርሃቱን ሲገልጽ፣ ለማ መገርሳ በርካታ አጃቢ ኦሮሞዎችን አስከትሎ ወደ ባሕር ዳር ነጎደ። በወቅቱ ጥረቱ ለበጎ ቢመስልም እኩይ ግብሩ የተጀመረውን የወጣቶቹን ግንኙነት ለማሰናከል መሆኑ ዛሬ ይፋ እየሆነ የምንሰማውና የምናየው ነው። ለማም ሆነ ዶር አቢይ እውቅና ያገኙት በወጣቱና በኢትዮጵያ ሕዝብ ብርቱ ትግል እንጂ ዛሬ ሁለቱ እንደሚያወሩት አይደእም። ጠቅላይ ሚኒስተር አብይ ታሪክ መሥራት የሚችለው ሕዝብን ሲያቅፍ እንጂ በመከፋፈል አይደለም። አጭር ቁምጣ ለብሶ መሥራት ለብልፅግና ሲያደርስ አጭር አስተሳሰብ ግን ያሰምጣል። ኢትዮጵያን እስከዛሬ ያቆያትና ባለታሪክ ያሰኛት እሴት የጋራ ታሪካችን ነው።

ኢትዮጵያ ድሃ ተብላ የምትፈረጀው ከፋፋይና ስግብግብ አመራሮች ቦታ በመያዛቸው እንጂ መሬቱ ሰብል አልሰጥ ወይም ሕዝባችን ሥራ ጠል ሆኖአይደለም፣ ለዚህ ሕዝባችንን ያበቃው የአመራር ድክመት ነው፣ ኢትዮጵያን ሲመሩ የቆዩ የወያኔ አመራሮች ሁሉንም የሥራ ዘርፍ በግላቸውና በቤተሰቦቻቸው በመያዛቸው ከዚያም ለአገርየሚገባውን ግብር ስለማይከፍሉ እድገት ሊመጣ አልቻለም። በወያኔ አመራር ባላገሩን አንድ በአንድ ማፈናቀል፣ ዛሬም ደገሞ በጅምላ ማፈናቀል ተጀምሯል። ማፈናቀሉ ከአዲስ አባባ ጀምሮ ወደ ጥቃቅን ከተሞች እንደሚዘልቅ ታከለ ኡማና ለማ መገርሳ እየተናገሩ ነው።

ይህን ጽሁፍ ለማዘጋጀት ያነሳሳን ሰሞኑን የተከሰተ ሁኔታ ለሕዝባችንና ለአገራችን አደጋ የሚያደርስ መስሎ ስለታየን ነው። ክስተቱ ይህ ነው፥ የካቲት 1 ቀን 2011 ዓም ዶር አቢይ እና ለማ መገርሳ አራት ኪሎ ትልቁ ቤተመንግሥት አዳራሽ በጣም ከፍተኛ ብዛት ያላቸው ኦሮሞዎችን ሰብስቧቸው ያወያዩአቸዋል፤ እነርሱም ለተሰብሳቢዎች የነገሯቸውን የኢትዮጵያ ሕዝብ ማወቅና የታቀደው ለሕዝባችን ጠቃሚ ነው ወይስ ጎጂ የሚለውን እንዲያስብበት በማለት ነው። በስብሰባው ላይ ከኦሮምኛ ተናገሪ በቀር ሌላ ቋንቋ የሚናገር መሳተፉ የተነገረ ፍንጭ የለም፣ ከዚህ መደምደሚያ በመነሣት ስብሰባው የኦሮምኛ ተናግሪዎች ብቻ ነው ለማለት ችለናል።

የመናገር ዕድል በመጀምሪያ የተሰጠው ለሕዝቡ ስለነበር ከተሣታፊዎች ከተሰጡት ጥቂቱን እንደሚከተለው እናቀርባለን፥ በሃይማኖት ደረጃ አንድ ቄስ ዛሪው ወደ ኋላ እይቀረን ነን፣የሃማኖት ሰዎች እንደሻማ ቀልጠው ብርሃን ማሳየት ሲገባቸው አንዲት መንደር እያቃተን ነው› እንኳንስ በአፍሪካ በኤውሮፓ በአመሪካ መሪ ያገኘን እንደት ተባብረን መሥራት አቃተን? ይህንን ድክመት ተገንዝቤ ለኦቦ ለማ ጠቁሜው ነበር፣ ማንኛውም ተጠያቂ አካል የተሰጠውን ኃልፊነቱን በብቃት የሚወጣ የለም፣ ሌላው ሙገሳውን ከአጠናቀቀ በኋላ በቅርብም ሆነ ከሩቅ ያለው ኦሮሞ በሚገኝበት ቦታ የኦቦ ለማና የአቢይ ተወካይ ነኝ ብሎ የመሥራት ግዴታ ይጠበቅበታል፣አንድ ሙስልም አባት ‹ኦሮሞ ያገኘሽውን ድል ካልተከባከብ ነገ ጠላቶችህ በከፋ ሁኔታ እንደሚያዋርዱህ አትዘንጋ በቃ ነፃ ወጥተናል» ሲል ማስጠቀቂያ ሰጠ፣እዚህ ላይ ጠላት የተባሉ እነማን እንደሆኑ ሲያስጠነቅቅ ጠላት ነው የሚባል ከቅርብ እንደሆነ ከሰጠው ቃል መረዳ ይቻላል። የብዙዎቹ ተሰብሳቢዎች ሐሳብ ተቀራራቢ ሆኖ ኦሮሞ የጀመረው የነፃነት ጥያቄ ከመጨረሻ መድረሱን ሲናገሩ እንዲህ በሉ ተብለው ከስብሳብዎች የተጠቆሙ ይመስላል ፣ በኦሮምያ ክልል ብቃት ያለው ሥራ እንዳተሠራም ብዙዎቹ በቁጭት ይናገርሉ። በተለይ ኦሮሞ ነፃ የመውጣቱ ጉዳይ ግቡን የመታ ቢሆንም ታች ድረስ ዘልቆ ምንም ሥራ እንዳልተከናወነ ከበርካታ ተሰብሳቢዎች ከረር ያለሂስ ቢሰነዘርም ሰብሳቢዎቹ አልትቀበሉትም። ውይይቱ ረጅም ጊዜ የፈጀ ሲሆን በመጨረሻ ለማ እና ዶር አቢይ የራሳቸውን ሐሳብ ሰጥተው ስብሰባው አበቃ።

ሁለቱ ሰብሳቢዎች ለተሰብሳቢው የሰጡት ምላሽ ተቀራራቢ ሲሆን ለኦሮሞ ነፃነት ቀደም ሚና እንደተጫወቱ በአያለው ጠቅሰዋል።አቶ ለማ ከጠቀሳቸው መካከል ከፊሉን መጥቀሱ ሐሳብ ለመስጠት ያመቻል ብለን ያመንባ ናቸውን እንደሚከተለው እንጠቅሳለን፥

1 በየእሥር ቤቱ ታስረው የነበሩትን በሙሉ ፈተናቸዋል፣ እኛ ከእሥር ያስፈታናቸው ኦሮሞን ብቻ አይደለም ዘር ጎሣን ሣንለይ ነው ያስፍታናቸው፣ ይህ ቀላል ግምት የሚሰጠው አይደለም።
2 ከተለያዩ አጎራባች ክልሎች የተፈናቀሉትን ከግማሽ ሚሊዮን በላይ በየከተሞች አስፍረናል ከነዚህም ከስድስት ሺህ በላይ አዲስ አባባ ከተማ ውስጥ ቤት ሠርተን ሰጥተናቸው በጥሩ ሁኔታ ላይ ይገኛሉ፣
3 በመዕራብ ኦሮሚያ በበኒሻንጉል ታጣቂዎች ተይዘው የነበሩትን ለማስለቀቅ መንገዱ ተዘግቶ ስለነበር ብዙ ችግር ፈጥሮብን በመጨረሻ ዶር አቢይ ኤውሮፕላን ፈቅዶልን የመከላከያ ሠራዊት ስንቅ ወስዶላቸው በአሁኑ ወቅት በጥሩ ሁኔታ ላይ ይገኛሉ፣
4 በዚሁ በምዕራብ ኦሮሚያ ማንነታቸው የማይታወቅ ከሺህ ጠመንጃ በላይ ከታጣቂዎች ቀምተው ብዙ ችግር እየፈጠሩ ናቸው፣ ስለሆነም እኛ እንዳልሠራን አትቁጠሩ፣

ዶር አቢይ የመለሳቸው

1 ስለ አዲስ አባባ ለተጠየቀው ፣አዲስ አባባ ያለ ጥርጥር ወደ አርሚያ ይጠቃለላል፣ ከአዲስ አባባ እንጀምር ብለን እንጂ በኦሮሚያ ክልል ውስጥ የሚገኙ ጥቃቅን ከተሞች ሣይቀሩ የኦሮሚያ ይሆናሉ፣

2 ለነፃነት የጀመርነው መሠረቱ ከታች ስለሆነ ፍጹም ሊቀለበስ አይችልም፣

3 ኦሮሞን ለመከፋፈል ሰሞኑን በእስልምና ስም እጅግ በጣም ብዙ ብር ይዘው ለመምጣት የተዘጋጁ ቡድኖች እንደተነሱብን ተጨባጭ መርጃ ደርሶናልና ተጠንቀቁ፣ ሤራውን ከመመከት ከተከፋፈልን ከመንዳትም አልፎ እስካሁን የተከፈለ መሥዋዕት ፍሬ አልባ ይሆናል፣

አስተያየት

የስብሰባውን ይዘት ስንመለከትው መልካም ይመስላል፣ በስብሰባው ላይ ከወንድሞቻችን ኦሮሞዎች በቀር የተሳተፉ አይመስልም፣ ጋዜጠኛ ለዘርም የለም፣ ስብሰባው ድብቅ ነው ማለት ይቻላል፣ ስብሰባውን እንዲተሳተፉ የተጋበዙትም በምስጢር የተጠሩ ይመስላል፣ ምክንያቱም እነ ዳውድ ኢብሳ እነ ጀዋር መሐመድ ወደ ስብሰባው ዝር አላሉምና።

ዘሬ ብዙዎቹ እንደማስፈራሪያ አድርገው የሚያቀርቡት .....እገነጣላለሁ.....ሌላውን እስብረዋለሁ......እኛ ከተገነጠልኩ የኢትዮያ ነገር አበቃ.......ወዘተ የሚባሉ ቃሎች ሲወረወሩ ይደመጣሉ። የማስፈራራቱ አንጃ ግራንጃ ዛሬ የትጀመረ ሣይሆን ረጅም ጊዜ ያስቆጠረ እምቦለለ ነው። ዘመን ያመጣቸው ጊዜ ሹመት የቸራቸው ጉልበታቸውን የሚሞክሩት በማፍረስ ላይ ነው፣ ጊዜ ባይከዳው ኖሮ መለስም የኢትዮጵያ ዋና ከተማ «ድረደዋ » ይሆናል ብሎ ቃዥቶ እንደነበር ከህልፈተ ሞቱ በኋላ ተወርቶ ነበር። ወያኔ ያነገሳቸው በሙሉ ለመለስ ኑዛዜ የተገዘቱ የመስል አዲስ አባባን ማፍረስ የአፍ መፍቻ ንግግር እያደርጉ ናቸው። አዲስ አባባ የተመሠረተችው በመላ የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦች ነው። ከጫካ አገር እያቆሰለ አዲስ አባባ የደረሰ ቀርቶ በሕዝብ የተመረጠ መሪም ቢሆን አ አባባን ሊያፈርስ አይችልም፣ ዛሬ የሕዝብ ውክልና የሌላቸው ስለአዲ አባባ ባይጨነቁ ይበጃቸዋል አዲስ አባባ የሚኖሩ ከሁሉምብሔር ብሔረሰቦች ሲሆን እንደቡራዩ ሕዝብ ተፈናቅሎ ከቦታው የሚጠለል አይደለም ፡፡አንገት የተፈጠረው አዞሮ ለምየት ነው ይባላል፣በአዲስ አባባ ላይ ሕዝብ አይደራደርም፣እጅግ በጣም ብዙ የኦሮሞሕዝብ አዲስ አባባ የኢትዮጵያ ዋና ከተማ መሆኗን ያምናል፣ ዛሬ የአዲስ አባባ ስም መለወጥ ወይም ወደ ኦሮሚያ መቀላቀል የሚወተውቱ መጪውን ምርጫ ለማሸነፍ የሚውተርትሩ ብቻ ናቸው።

ሰሜን ም ዕራብ ኢትዮጵያን ለሱድን የሰጡት፣ ከጋምቤላ መሬት ላይ ያስፈሯቸው ሱዳኖች ሁሉ የኢዮጵያ ሕዝብ ውክልና በሌላቸው ገዢዎች ናቸው፡፡ ዶር አቢይም ሆነ ለማ ስለአዲስ አባባ ለዉሳኔ ባይቸኩሉ ይበጃል። የኢትዮያ ሕዝብ ብሔራዊ ፓርቲ እና የኦሮሞ ሕዝብ ንቅናቄ ለኢትዮጵያ አንድነት በጉዳይ ላይ በሰፊው በነጋገር ለመላ የኢትዮጵያ ሕዝብ ይበጃል ብሎ ያመነውን ያቀረቡት የኢትዮጵያ ድብቅ አጀንዳው ግልጽ ሆኖለት እንዲወያይበት በማመን ስለሆነ የየድርሻችን መወጣት ይጠበቅብናል።

ሙሉን ውይይት በኦሮምኛ ለማየት ይህንን ይጫኑ

https://www.youtube.com/watch?v=TbjvUSeLJ-A&feature=youtu.be

አንድነታችን ለዘለዓለም ተከብሮ ይኖራል !!

በአባቶቻችን ደም ፍሳሽና አጥንት ክስካሽ እስከ ዛሬ የኖረች ለወደ ፊትም ትኖራለች !!

| | |
|---|---|
| ኢሕብፓ<br>EPNP<br>የኢትዮጵያ ሕዝብ ብሔራዊ ፓርቲ<br>ETHIOPIAN PEOPLE NATIONAL PARTY | ኦሕንኢአ<br>OPMEU |

EPNP.INFO

ኢሕብፓ
EPNP
የኢትዮጵያ ሕዝብ ብሔራዊ ፓርቲ
ETHIOPIAN PEOPLE NATIONAL PARTY